# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 45 ቁ 2 — <u>ጥቅምት/ ኅዳር 2012</u>


## <u>ማጠፊያ ላይ ወዴት ከዚያስ ወደየት</u>

በጊዜ ሂደት በህይወት ማጠፊያ ላይ ወይም በሀገር የነገ ዕጣ ወሳኝ ወቅት ላይ ስንደርስ፤ ሁናቴው ለድምዳሜ አልታጠፍ ብሎ ሲያስቸግር የት ደርሰናል ወደየትስ ልንጓዝ ነው፤ ምን አማራጮች ተደቅነውብናል ብለን በጥሞና መመርመር ግድ ይሆንብናል፡፡ ይህ ደግሞ ስሜታዊ የሆነ ድምዳሜን፤ ቀቢጸ ተስፋን ያነገሰ ዕይታ ሳይሆን ተጨባጩን ሁኔታ ረጋ ብሎ መገምገምን ይጠይቃል፡፡ አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ በቁንጮነት የሚመራው ግለሰብ ያልሆነውን ሆነ ብሎ መመኘት፤ የሰው ህይወትና አገር እያጠፋ ከሰማይ የወረደ ሙሴ ወይም የአገር ጀግና ብሎ መቃዠት፤ ቅልጥ ያለ ዘረኛ ሆኖ የወያኔን ከፋፋይ ሕጎችና አዋጆችን ለመሻር አሻፈረኝ በማለት ደርቆ እየቧረቀ እያለ ሀገር አድን ነው፤ ለውጥ አምጪ ነው ብሎ መደምደም በሰከነና በበሰለ አእምሮ ተጨባጩን ሁኔታ በጥሞና ማየትና መገምገም ሳይሆን ሀገርን ለጥፋት የሚዳርግ ቅዠት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ግለሰቡን ያመጣብን ፈረንጅ ቢያወድስ ቢሸልም ምንም የሚያስደንቅ አይደለም፤ አስገራሚ የሆነው ግን ንጹሃን ዜጎች በግፍ ከታረዱና ከተጨፈጨፉ በኋላ መንጋዎችን የለቀቀባቸው ሰው ለፍርድ ይቅረብ ቢያንስ ይወገዝ ማለቱ ቀርቶ፤ የተፈጁት ወገኖች ከመቅጽበት ተረስተው ወንጀለኛውን አወዳሾች ሲንጫጩ መስማት መገደዳችን ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ መቸም፤ ለቀን ሀሴት እንኳ ሳይታደል፤ አፈር ገፊና ገፈት ቀማሽ ሆኖ ዘመን አሳልፎ ለትግል ሲነሳ እያደናቀፉት፤ መፈክሩን ውሃ እየቸለሱበት ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ኑሮን መቀበል መሸከም ህይወት ሆኖበት ዘመናት ማሳለፉ ለማንም ምስጢር አይደለም፡፡ የዛሬ የታሪክ ላጲሶች ሊክዱ እንደሚፈልጉት ሳይሆን መብቱን ተነፍጎና ፈርጀ ብዙ ጭቆና ተሸካሚ ተደርጎ መቆየቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ለመሠረታዊ መብትና ለእኩልነት ለዴሞክራሲና ብልጽግና ያደረገው ተጋድሎ ሁሉ ታፍኖበታል፡፡ ጊዜውን ጠብቆ የፈነዳው የየካቲት 66 አብዮት አመጻኛ ትውልድ ያመጣው ሳይሆን ለለውጥ ዝግጁ ያልሆነው ሥርዓት በራሱ ላይ ያመጣው ነው፡፡ ከትውልዱ አብዮት በፊት በሥርዓቱ ላይ ተስፋ የቆረጡ በርካታ የመፈንቅል ሙከራዎች ተካሂደው የነበረ ሲሆን የአፄው አገዛዝ ከነዚህ ትምህርት ወስዶ ሊሻሻል ባለመቻሉ አብዮትን በራሱ ላይ አምጥቷል፡፡ ብዙሃኑ አርሶ አደር ወደ ጭሰኝነትና ገባርነት በመለጋቱ መሬት ለአራሹ ጥያቄ ወሳኝና አንገብጋቢ ሆነ፡፡ ይህ ጥያቄም ከእኩልነትና ብሔር ጥያቄ ከተባለው ጋርም በመቆራኘቱ ለለውጥ ፈላጊዎች በዝምታ ሊታለፍ የማይችል የአበጠው ይፈንዳ ጉዳይ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር አልነበረውም፡፡ እስከዛሬም ያልተፈታው ይህ ዐቢይ ጥያቄ ዛሬም ሊፈታ የሚችለው አርሶ አደሩ የመሬቱ ሙሉ ባለቤት ሲሆን መሆኑ እየታወቀ የመጡት ሥልጣን ይዘው የቆዩ አገዛዞች ሁሉ በአርሶአደሩ ላይ

ባላባት ሊሆኑ በመፈለጋቸው ችግሩ መፍትሄ አጥቶ ቀጥሏል፡፡ ተራማጆችና ኢሕአፓም የጠየቁት መሬት ለአራሹን እንጂ መሬት ራሱን መንግሥት ለሚል ተቋም ይተላለፍ የሚል ባለመሆኑ ባላባታዊ ሥርዓትን ቀየርን ያለውም ሆነ እሱን የተካው አገዛዝ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ባለመቻላቸው እስከዛሬም ይህ ሕዝባዊና ዘመን ያስቆጠረ ጥያቄ ምላሽ አላገኘም፡፡ የዘንድሮዎቹ ይባስ ብለው የኬኛ ኬኛ አገዛዝ ስለሆኑ መንጋ አሰማርተው ሕዝብን ከመሬት በገፍና በግፍ ማፈናቀል፤ መሬት መቀማትና የመዲናዋን ስም እስከመቀየር ድረስ የሚውገረገሩ በመሆናቸው በዚህም በኩል ሰቆቃችን ቀጣይ ሆኖ ብዙሃኑን እያስለቀሰ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ማለትም በመሠረቱ ሕዝቡ በግልጽ ብዙ ምርጫዎች ኖረውት በዴሞክራሲያዊ መንገድ ወሳኝና መራጭ የሚሆንበት ሂደት አልተከሰተም። ይህም በመሆኑ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ተረማምዶ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሰረት ኢሕአፓ በ1967 አካባቢ ያቀረበው የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ከዚያን ጊዜ እስከዛሬ ከገዢዎች ያገኘው መልስ አሉታዊ በመሆኑ፤ ሕዝቡ ተሰባስቦና መክሮ በነፃ ምርጫ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መስርቶ ለመሸጋገር ባለመቻሉ፣ መብት በመነፈጉ፤ አንዱ አምባገነን በሌላ እየተተካ እስከዛሬ የአምባገነኖች ሰለባ ሆነን ቀጥለናል፡፡ ዛሬም የቀረበውን ሕዝባዊ የሽግግር ሂደት ጥያቄ ዘረኞች ጆሮ አንሰጥም ብለው 27 ዓመት የወዘፉብን የግፍ አገዛዝ ሊቀጥሉብን ወስነው ውጤቱን ከዛሬ ለምናውቀው አሻራ ቢስ ወያኔያዊ ምርጫ ሊዳርጉን ተነስተዋል፡፡ ሽግግር እያደረግን ነው በማለት ለመስበክ የሚጥሩት ሁሉ ቅጥፈት ለመሆኑ ማንም ለክርክር የሚፈልገን ሊኖር አይችልም፡፡ የምን ሽግግር፤ መቸስ? ወደአለፈውና ወዳለው የምንንደረደረው እየተካሄደ ነው የተባለው ለውጥ የቃላት እንጂ የሐቅ አለመሆኑን ለማስረገጥና የዛሬው ከትላንት ጋር ተወራራሽና ተመሣሣይነት ያለው መሆኑን ለማቅረብም ነው፡፡ ለየት ደርሰናል ጥያቄያችንም ጉዞአችንን መቃኘቱ አስፈላጊ ነውናም ነው፡፡ መፈክሮቻችን ዘመን አሻጋሪ ሊሆኑ የበቁት የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እንደ ሞኝ ለቅሶ መልሶ መልሶ ሆኖብን አመርቂና ስር ነቀል ለውጥ ህልም ሆኖ በመቅረቱ ነው፡፡ የዘንድሮዎቹማ መሠረታዊ ለውጥ ማለትን ሁሉንም ማውደም ነው የሚል ሽውራራ ትርጉም ሰጥተው ሳይነጋ የታሪክ ቅርሶችን በማፍረስና በማቃጠል ሰንደቅ ዓላማችንን በማውደምና በመቅደድ ተግባር ላይ መሰማራታቸው የታወረ ልብ ተሸካሚ መሆናቸውንን ለዓለም ሁሉ አሳይተዋል፡፡ ከዓመታት በፊት የኑሮ ውድነት አደቀቀን፤ ዋጋ ይቀነስ፤ ደሞዝ ይጨመር ስንል እንጮህ የነበረው ዛሬም ወሳኝ ጥያቄ ሆኖ ሀገራችን በዓይናችን ሥር እየተበዘበዘች፤ ጩኸታችን ሰሚም አጥቶ ሌቦች በባሱ ጅቦች ተተክተው ከማየታችን በላይ የዛሬ 16 ዓመት በታህሳስ ሶስት በእነ ባርናባስ፤ መለስ ዜናዊና አባይ ትዕዛዝ የተገደሉትን ከሺ ያላነሱ አኝዋኮች ዛሬ ብዙ ሺ አማራዎች፥ ጌዴዎች/ጋሞዎች፥ አፋሮች፥ ወላይታዎች፥ ...ወዘተ ደማቸውን ገብረው ማጀባቸውንም ታዝበናል። ይህም የሹሞቹን አመጣጥና ከይሲ ግባቸውን በሚገባ ጠቋሚ ቢሆንም ሆድ ከሀገር እየቀደመ ብዙዎች ጆሮአቸው ላይ ተኝተው ለዘረኞቹ ጊዜ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ለሥልጣን እንደበቁ በሾሚቻው ኃይላት ትዕዛዝ ለሻዕቢያ የሚጠቅም ሰላም ተብዬ ስምምነት በማድረግ ጉርሻቸውን ከአረቦቹ ተቀብለው የክህደት ጉዟቸውን ተያያዙት፡፡ በጸረ የመኑ የጥፋት ጦርነት የሳውዲና ኤሚሬትስ ደጋፊ ሆኖ አሰብን ሁሉ የሸጠላቸው ሻዕቢያ ሰላም ተመሰረተ ተብሎ ማዕቀቡ ሁሉ ተነሳለት፤ ተጠቀመ፡፡ የኤርትራ ሕዝብ ሰቆቃ ምንም ሳይቀንስ የቀጠለ ሲሆን እፍ እፍ ያሉለትም ድንበር መከፈትና ንግድ በዚያው ወዲያውኑ ከስሞ ቀርቷል፡፡

በሕዝባዊ ትግላችን ሂደት ዋናና መሠረታዊ ጥያቄ ሆኖ የተገኘው የሥልጣን ጥያቄ መሆኑ የሚያስገርም አይደለም ፡፡ ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት የሚለው የተራማጆች መፈክር የችግሮችና የቀውሶችን ማስወገጃ መንገድ ያመለከተ ሲሆን መፍትሄውም ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት መሆኑን ያስረገጠ ነበር። የፖለቲካ ሥልጣን የሚሰርጸው በምርጫ ነው ወይስ

በአመጽና በጠመንጃ የሚለውን ግን ሁሌም መላሹ ገዥው ሥርዓት በመሆኑና፤ የአጼውም አገዛዝ ለሰላማዊ መንገድ ጋሬጣ በመደርደሩ አብዮትን በራሱ ላይ አመጣ፤ እስካሁን ሊደገም ያልቻለው የየካቲት 66 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሥርዓቱን ጠራርጎ ጣለው፡፡ የሕዝብ የድርጅትና የድሉን ማስከበሪያ አቅም ደካማ ነበርና የታጠቀውን ኃይል የሚመራው የመኮንኖች ቡድን ሥልጣንን ወሰደና የሕዝብን የጊዚያዊ የሽግግር/ሕዝባዊ/ መንግሥትን ጥየቄ አልቀበልም በሚል በኃይል በሕዝብ ላይ ተሰየመና ፋሺስታዊ አስተዳደሩን አሰፈነ፡፡ ያኔም እንደዛሬው ከርስ አስቀዳሚና አድርባይ ግለሰቦችና ቡድኖች ደርጉን ደግፈው በመቆም በታጋዩ ሕዝብና በኢሕአፓም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ፡፡ ያኔም ሲሰጡ የነበሩትን ማጠየቂያዎች የዛሬዎቹ ዘረኛ ሹሞች ሲደጋግሙ መስማታችን አልቀረም። ሕዝቡ አልነቃምና አድሃሪዎች ድሉን ይነጥቁታል፤ እኛ እናሻግራችኋለን፤ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ያስፈልጋል፤ ዲሞክራሲ ቅንጦት ነው፤ ድንበር በወታደሩ ነው የሚከበረው፤ ...ወዘተ ወዘተ የሁሉም ይዘትና ትርጉም ግን እኛ ወይም እኔ ሥልጣኔን ማስረገጥ አለብኝ ለሚለው ምክንያት ነው፡፡ ወያኔም ሥልጣን በያዘበት ወቅት የሽግግር መንግሥት መሠረጥኩ ብሎ የነበረው ቲያትር መራራ ውሸት መሆኑ ወዲያውኑ የተረጋገጠ ሲሆን ዛሬም ሹሞቹ እናሸጋግራለን ይበሉ እንጅ ሁሉን ያሳተፈና ሕዝባዊ መሠረት ያለውን የሽግግር ሂደት የተቀበሉም ሆነ ተግባራዊ ያደረጉ ሳይሆን እነገደይና ስብሃትን ተከተው እነኡማና መገርሳን በዚያው የዘረኛ ውሃ ልክ የተኩ ናቸው፡፡ ስለዚህም መሠረታዊው የመንግሥትና የሥልጣን ጥያቄ አሁንም ሕዝባዊ ምላሽ አላገኘምና ቀውስና ብጥብጥ፤ ትግልና አድማ፤ አመጽና እንቅስቃሴ ቢቀጥል ከቶም አያስገርምም። በግርግር ጅቦቹ ሀገራችንን እንዳይቦጭቋት ነው የእኛ ስጋታችን።

ሕዝብ የመሬቱ፥ የመብቱ፥ የሥልጣኑ ባለቤት ሳይሆን ቢቆይም፤ ትግሉ ቢዳከምም መብቱን ለማስከበርና ሀገርን ለመጠበቅ ሳያቋርጥ ታግሏል። የወያኔን ከፋፍለህ ግዛና ሕዝብን ከሕዝብ የማጋጨት ሴራ ተቋቁሟል፡፡ ዛሬ ያሉት ዘረኛ ቡድኖች ከወያኔ ጋር እጅና ጓንት ሆነው መቆየታቸውን የረሳ ሊኖር አይችልም፡፡ የአውሬዎቹ ሹም የወያኔ ዋና ሰላይ ሆኖ የተቃዋሚ ኃይላትን ሊያዳክምና አፍ ሊያዘጋ 27 ዓመት ሙሉ ያገለገለ የተለጣፊው ኦህዴድ ዋና መሪ እንደነበር ምን ስም ቢቀያይር ሊያስረሳን የሚችለው አይደለም። የወያኔም አገልጋይ በነበረበትም ግዜ ከኢትዮጵያ ተገንጥለን ኦሮሚያን እንመስርት ለሚለው ኦነግ ሰርጎ ገብ ሆኖ በመስራት ምስጢር የተባለውንም በእጅ አዙር ለሻዕቢያ ሲያስተላልፍ እንደነበርም ዛሬ ተጋልጧል ፤ ራሱም አምኗል፡፡ በክህደት ሊከሰስ የሚገባው ሰው የሀገር መሪ መባሉ ራሱ ምንኛ የሀገራችን ፖለቲካ ልጓም ከእጃችን እንደወጣ በሚገባ ጠቋሚ ነው፡፡ አፍ ሌላ ልብ ሌላ እንዲሉ ሸንጋዩ ሹም ውስጡ ሲገለጥ ዘረኝነትን፥ ክህደትን፥ ሀገር ጠልነትን አስልቶ የያዘ መሆኑ ይታያል፡፡ ይህንንም ለማሳየት ጊዜም አልፈጀበትም፡፡ ልብሳቸው ቡትቶና ድሪቶ በሆነባት መከረኛ ሀገር የሕዝብን የድህነት ሁኔታ ለማጥፋትና የወያኔን ሥርዓት ለማስወገድ በመጣር ፈንታ ጸረ ሕዝብ ጽንፈኞችን አምጥቶና ያለቁጥጥር በነጻነት እንዲፈነጩ ፈቅዶ ድሃውን ሕዝብ ፈጀው፤ ፈጁት፡፡ ጉንጭ አልፋ ሸንገላን መሳሪያው አድርጎ፤ ትሁት ለመምሰል እየተቅለሰለሰ ድሃውን ሕዝብ አሳረደው፤ በሚሊዮኖች ደረጃ አፈናቀለው መንገድ አዳሪ አደረገው፤ በረሃብ አስጠበሰው፤ ሀገራችንን ባዲሶቹ ጅቦች አዘረፋት፤ አስቦጨቃት፤ የሀገርን ሉዓላዊነት አስወሰደ፤ ክብሯንም አዋረደ። የአንድ ሰው ጥፋት ሳይሆን ባዕዳን የተከሉብን የዘረኛው አገዛዝ ወንጀል ነው፡፡ ሁሉም መጠየቅ መወገድ ያለባቸው ለዚህ ነው፡፡

ባዕዳን ሰልፋቸውና ስምሪታቸው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ መንግሥትና ሥርዓት በምንም ዓይነት የሕዝብ እንዳይሆን ነው፡፡ ይህን መፈለጋቸው አይፈረድባቸውም፤ ታላቅነታቸው በአፍሪካውያን ብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ነው፤ ሀብታቸው ከአፍሪካ የተነጠቀ ነውናም፡፡ ፓትሪስ ሉሙምባን በኮንጎ አስገድለዋል፤ የአፓርታይድን አገዛዝ ደግፈው ኔልሰን ማንዴላን ሽብርተኛ ብለውም ወንጅለው ነበር፤ ኤርነስት ኡዋንዴ፥ ሳሞራ ማሼል፥ አሚልካር ካብራል የነሱ ሰለባዎች ናቸው፡፡ የምዕራብ

አፍሪካን ሀገራት ፈረንሳይ ባትበዘብዝ ኖሮ የወደቀች ሀገር ትሆን ነበር የሚለውንም የፈረንሳይ ፕሬዚዳንቶች ሳይቀሩ ያመኑት ነው፡፡ አሜሪካ ጋዳፊን በማስገደልዋ ስህተት መፈጸሟን አባማም ሳይቀር አምኗል፡፡ ለአፍሪካ ሕዝብ ሙብትና ነፃነት፤ ለብሔራዊው ደህንነትና ክብር የሚቆም ሁሉ ውሎ አድሮ ሳይሆን በቅጽበት የፈረንጆቹ ጠላት ይሆናል። አረቦች ደግሞ የራሳችው ብሔራዊ ጥቅማቸው በረጅሙ ከኢትዮጵያ ተጻራሪ ሆኖ በመቆየቱ ቢያንስ በነሱ ግምት የኢትዮጵያን ክብር የሚያስጠብቅ መንግሥት በኢትዮጵያ እንዲኖር ከቶም አይፈልጉም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ ለመሰባበር ተባብሮ በማመጹና የዚህ ትግል መጨረሻው ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ሙብት የሚመች ውጤት ለማምጣት ቆርጦ መነሳቱን የተገነዘቡ ባዕዳን በሁኔታው ደንግጠው በምስጢር መሰባሰብና መዶለት ተሰማርተው በሚያሳፍር ደረጃ ኢትዮጵያውያንም ተሳታፊ በሆኑበት ሴራ የወያኔን ዋና ሰላይ ማለትም ሹሙን መርጠውና ኮትኩተው ለሥልጣን አብቅተውታል። ወያኔንም በቅቶሃል ጥግ ያዝ ያሉት እነሱው ናቸው፡፡ ሹም ሊሆን የተመረጠው ግለሰብ አቡ ዳቢ/ዱባይ ሄዶ ከኢሳያስ ጋርም በምስጢር መገናኘቱን በወቅቱ ያጋለጥነው ጉዳይ ነው። በፕሮፓጋንዳው መስክም የፈረንጆቹ ራዲዮና ቴሌቭዥኖች በስፋት ለማሻሻጥ ተረባርበዋል፤ ኢሕአፓም ላይ ዘምተዋል፡፡ ጽንፈኞቹን በአማካሪዎችም አጅበዋል፡፡ ባዕዳን ኢትዮጵያን አንበርክከው ተገዥ ማድረግ ይፈልጋሉና ፤ ሀገራችን በአፍሪካ ያላትን የፖለቲካ ክብደት ያውቃሉና ሁሌም ሊያንበርክኩዋት ዝግጁ ናቸው፡፡ ይህን ደግሞ በተለይ ኢሕአፓን ማግለልን ይጠይቃልና ሹሙ ኢሕአፓን ለማራቅ ትዕዛዝ የተሰጠው በነሱው ነው፡፡ ያመቸናል፥ ይጠቅመናል ብለውም በፖለቲካ ምድረበዳ ሲዋልል የነበረውን ከንቱ የአንጃ ቡድን ኢሕአፓ ብለው በማስገባት ሁለት ወፍ ባንድ የባንዳ ድንጋይ ገደልን ብለው ፈነደቁ፡፡ ዛሬም ይህ ርካሽ ቡድን ህጋቸው የሚፈልገውን ቁጥር ባያሟሏ እንኳን አሟልቷል ብለው ሊመዘግቡት፤ ሊጠቀልሉት ወይም የምርጫ አጃቢ መጋዣ ሊያደርጉት ወስነዋል፡፡ ውድቀቱ ከወዲሁ ግልጽ ቢሆንም ሲዳከሩ የምናያቸው ይሆናል፡፡

የወያኔን ሥርዓት በነስብሀት ሳይሆን በነመገርሳ ተተክቶ ለውጥ የመጣ አስመስሎ ማስቀጠሉ አላማቸው በመሆኑ ተረባርበው የሕዝብ ስር ነቀል ለውጥ ጥያቄ አመጽ እንዳይሳካ ማድረግ ችለዋል፡፡ የነበረው ትግል ሕዝባዊና ኢትዮጵያዊ ሳይሆን የጎጥና የጎሳ ነው ብለው አሁንም እያቀረቡ ያሉት ትንተና ሐቁን ለመሸፋፈን መሆኑን ዛሬ ሁሉም አውቆታል፡፡ ፈረንጅ አምላኪዎች የነሱን ከንቱ ወሬ ቢደጋግሙም ወደ ጎጥ የመለሰን ቅልበሳው እንጂ ትግላችንማ፤ ስንቱ የጋራ ደሙን የገበረበት ትግልማ ኢትዮጵያዊና የሽግግርን ሂደትና ሕዝባዊ መንግሥትን ባጭሩ የሥርዓት ለውጥን የጠየቀ ነበር፡፡ ዛሬ ቄሮ ብለው በወንጀልና በጥበት ሊቀይዱት የተነሱት ትግል የኢትዮጵያዊ ትግል የሆነ የኦሮሞ ወገኖቻችን ትግል እንደነበር የምናውቀው ነው፡፡ ወጣም ወረደም ግን የሹሞቹ አገዛዝ የኦህዴድ ኦዴፓ ጽንፈኛና ዘረኛ አገዛዝ ለመሆኑ ሳይቆይ የተጋለጠ መሆኑ ለሕዝብ ሁሉ ግልጽ ነው፡፡ ቡራዩ፥ ለገጣፎ፥ ቤኒ ሻንጉል፥ አጣዬ፥ አዋሳ፥ ጌዴዎ፥ ...ወዘተ ማለት ዛሬ አያስፈልገንም። ሰው ማለት ሰው የሚሆን ሰው የጠፋ ለት ቢባልም ብዙዎች ሕዝብን ለሰቆቃ አጋልጠውና ጽንፈኞችን ደግፈው መከራችንን አባብሰውታል፡፡ ዛሬ በጽንፈኞቹና በሹሙ መሃል ልዩነት ሊገነቡ ወይም እዩ ሊሉን የሚፈልጉት ሁሉ ራሳቸውን አታለው ሕዝብን የሚያደናግሩ ብቻ ናቸው። ተማርን አወቅን ብለው ግን በሚያሳፍር ደረጃ ድድብና አንጸባርቀው በተጨባጭ ተግብሩ ጠባብና ሕዝብን ጎጂ የሆነውን ሹም ዛሬም ከተጋለጠ በኋላ የሚያወድሱ ምሁር ተብዬውች ወደዱም ጠሉም በጸረ ኢትዮጵያነት ቢፈረጁ የሚያስገርም አይሆንም፡፡ ታርካቸውና ጀርባቸውን ገለጥ አርገን ብናየው የክህደት ጀርባቸው ያፈጥብናል፡፡ ለመሆኑ ከደርግ እነማን ተባበሩ? ከነወያኔስ ጋር ገጥመው እነማን ተሰለፉ? እነማን ታሰሩ፤ ታገዱ እነማንስ በሀገር ፈነደቁ፤ ነገዱ፤ ሊንደላቀቁ ተነሱ? ሚኒስቴር፥ ዳይሬክተር፥ ...ተብለውስ ተሾሙ? ከበሩ፤ ኢትዮጵያን በዘበዙ፤ በአጭሩ እነማን ወየኑ? እነዚህ ሁሉ ዛሬ ያላቸውን አሰላለፍ ማጤን የሚገባ ነው፡፡ የክህደት ጂንሳቸው ሰልፋቸውን ሁሌ የውርደት አድርጎት ዛሬም የሹሙን ጫማ ሳሚና ተጎንባሽ ሆነው በሰማዕት ደም ያላግጣሉ፡፡ ነግ አይመጣ መስሏቸው

ከአሳማው እርያው ጭቃ ሲገቡ መካሪም ሽማግሌም አልሰማ ብለው ሀገርና ሕዝብን ክደው ነውና መጨረሻቸው በጣም መጥፎ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለንም።

መደመር ይሉናል መገደሉ ሰፍኖ፤
ዋሾና ቀጣፊው የክብር እንግዳ ሆኖ።

የተባለው ሰቆቃችንን ገላጭ ሆኗል። ከጠዋቱ ብለነው ነበር ብንል ብለን ነበር አይሆንብንም። አማራና ክርስቲያንን በሜንጫ መጨፍጨፍ የሚለውን ጭራቅ፤ ማለትም ራሳቸውን የሕዝብ ዓይንና ጆሮ ብለው ይመጻደቁ የነበሩ መድረክ ሰጥተው ሲያዳንቁት የነበረው ውርጋጥን የክብር እንግዳ ብለው ሹሞቹ ጋብዘው አምጥተው አቅፈውት ሲፈነድቁ ስናይ ወገን ጠንቀቅ በል ያልነው አለምክንያት አልነበረም። ወዲያውኑም ወደ አሥመራ ተጉዘው ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚለውን ኦነግ አቅዋሙን ሆነ መርሃ-ግብሩን ሳይቀይር የክብር እንግዳ ብለው አስገቡት፤ ነፍስ ዘሩብት። ሳይውል ሳይድርም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ ዘመቻ ከፈቱ። ቃል ወደ ተግባር ተቀይሮ በቀጥታ ዘር ማጽዳትና የሕዝብ ፍጅት እውን ሆነ፤ አማራው፥ ጋሞው፥ ጌዴዎ፥ ወላይታ፥ አፋር፥ ...ወዘተ ብለው መነጠሩ። ይህ ሁሉ ግፍ እየታየ ከርስ አደሮች ሹሞቹን በማወደስ ቀጠሉ። በረድ ብሎላቸው የነበረው ዛሬ ፈረንጆቹ ባሪያቸውን ሸለሙ በሚል እንደገና አገርሽቶባቸዋል። ያው መታገሉ ግዳጃችን ነው። የጎጥና የጎሳ ችግርን አራግበው እንደ ሰደድ እሳት ሊያደርጉት የተነሱት ሹሞቹና ጠባቦቹ ናቸው እንጂ ሕዝብ አይደለም። አንድ ውርጋጥ ግለሰብ ሳይሆን አገዛዙ ነው። ስም ቢቀያይሩ ሊሸፍኑት የማይችሉት ሐቅ ይህ ነው። ተዋሃድን ብለው ዘይትና ውሃ ሆነው መገኘታቸውን ሊሸፍኑ ቢጥሩም ዘላቂ አይደለም። የአድርባዮቹ መንጋ ባንድ ቢጨፈለቅ ማንንም አያሳስብም። ወያኔም ኦነግም እንዲሁ ሎሌያቸውን ይሰበስባሉ። ሽኩቻው የዘረኞች ነው። ማን አሸናፊ የሚለው የሚፈታው ባለጉልበት ማነው በሚለው ነው። ምርጫ ተብዬው እንደበፊቱ ቧልት መሆኑ አይቀርምና ማንም ተመረጠ ማን የሕዝብ ሀቀኛ ወኪል ሊሆን አይችልምና የሚፈሩት ትግልና አመጽ ቀጣይ ይሆናል። ትላንት የቀሙት ድል ነግ የሕዝቡ፣ የእኛ መሆኑ ሲገመት እነሱም በሥልጣን ሹኩቻ እርስ በርሳቸው የሚጠፋፉ መሆናቸውን መናገሩ ነቢይ መሆንን የሚጠይቅ አይደለም።

የአሁኖቹ ገዥዎች ለሥልጣን ከበቁ በኋላ ይህ ነው የሚባል ገንቢ ተግባር ሲፈጽሙ አልታዩም። ሀገራችንን ከማመስና የስጋት ምድር ከማድረግ ውጭ የፈየዱት የለም። ሹሙ በርግጥ በርካታ የድርጅቱ አባሎችንና የብሄሩ ተወላጆችን ሾሟል፤ ጠቅሟል፤ ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ግን ከዚህ ያገኘው ምንም የለም። የቄሮው ቡድን መሪ ነኝ የሚለው ወሮበላውና ግብረአበሮቹ ከሂደቱ አተርፋለሁ ብሎ የቋምጡት የሚሆንላቸው አይደለም። የብልጽግና ፓርቲ የተባለው የሹሙን የግል የበላይነት ሊያሰፍን የተጠነሰሰ መሣሪያው ነው። ነገሩ የገባቸው የሹሞቹ ጽንፈኛ ጓደኞቹ አንቀበለውም ማለታቸው የሚጠበቅ ነው። አድርባዮች በፓርቲው ቢገቡም የሚያመጡለት ሰፊ ጥቅም የለም። ሁሉን እስረኛ ፈታሁ ብሎ እንደሚዋሸው ሁሉ ኢምንቶችን አቅፎ ብዙዎችን አሳተፍኩ ብሎ መቅጠፉም መጠበቅ ያለበት ነው። ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ። የተበደለችና የተጎሳቆለች ሀገር ይህን ቧልት የምትችልበት ጎንና ጊዜም የላትም። ግን አዙሪቱ ጀምሯቸዋልና መመለሻቸው ሕዝብ በትግል ሲያሳፍራቸው ብቻ ነው። የሕዝብን የትግል መፈክር ቀምቶና በርዞ ከጥቅም ውጪ ማድረግ የጨቋኞች የሁሌም ልምድ ነው። የተጠየቀውን ሕዝባዊ መንግሥት አግደው ኢህድሪ/ኢፍድሪ ሲሉን ከርመዋል። ሽግግር ስላልንም አሁንም የሽግግር ሂደት ያለው አስመስለው ሊጓዙ ይጥራሉ። አለቆቻቸው ፈረንጆችም ሽግግር እንዳለ አስመስለው ይቦተልኩላቸዋል። መሬት ለአራሹ በማለት የታገልንለትን ያልተሟላ መፈክርም ቅራሪውን ሊያወጡ መሬት

ለወጣቱ በማለት ሊያስተጋቡ የፈለጉም መሃይሞች ወደ መድረክ ብቅ ብለዋል፡፡ ለምን ለወጣቱ ብቻ ? ለዚህም ነው የትግል መፈክሮቻችንን አይቀሙን፤ ለምን ወገን እንደተሰዋ አንዘንጋ፤ ወደሌላ አቅጣጫም አይውሰዱብን ብለን ሁሌም እምናሳስበው፡፡ የወቅቱ አንገብጋቢ መፈክር ሁሉን አቀፍ የሽግግር ሂደት እውን ይሁን ወደ ሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ እንጓዝ የሚለው ነው፡፡ ዛፍ ተከላ፤ መንገድ ጠረጋ፤ የራስና የሌሎች ሾፌር መሆን፤ ቤተ መንግሥት ማፍረስን ምኒሊክ ስሙ እንዳይጠራ ማድረግ፤ ቤተ ክርስቲያናትን ማጋየት፤ ዘር ማጽዳትና ፍጅት ማካሄድ፤ እርባና ቢስ ምርጫ ብሎ ገንዘብና ጉልበት ማባከን፤ ...ወዘተ ዋናና ጠቃሚ ስምሪቶች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ከዓመት በላይ ሀገር ታመስ እንጂ አልተረጋጋም፤ ሹሙና ጓደኞቹ በሃይማኖት በቋንቋ በብሔር ከፋፍለው ሊያፋጁን ታከተው ሰሩ እንጂ ሕዝብን አንድ አድርገው ሊጓዙ ጭራሽም አልፈለጉም፡፡ ሹሙ በተለይ በተነፈሰ ልክ ሀሰትን እሚያነግስ መሆኑ ተጋልጧል፡፡ በስሌታቸው የናቁትን ሕዝብ አላስገቡምና ይህ የሚያወድማቸው ስህተት ሆኖ በመከሰት ላይ ነው፡፡

ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራምና በነበረው ሁኔታና አሁን ባለውም ላይ ግንዛቢያችንን አስቀምጠን ነገ ምን ይጠብቀናል? ምንስ መሥራት አለብን? እንዴትስ ሀገር ማዳን አለብን? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት በዋናነት ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም ወያኔ ወደነበረበት ለመመለስ በግልጽም በድብቅ ሴራው ሲፍጨረጨር እያየን ነውና ጽንፈኞች ለራሳቸውም ለሀገርም የማይበጁ ማፈሪያ ጉዶች ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር ሊኖር አይገባም፡፡ የታሪክ አተላዎች ሁሉ እንደ ጨጎጊት አገዛዙ ላይ መጣበቃቸው በራሱ በቂ መረጃ ነው - ግም ለግም አብሮ ሊያዘግምብን ተሰባስቧል። ሹሙና መሰሎቹን እነማን እየደገፉ ናቸው ለሚለው ምላሽ ስንሰጥ የሰው ታናሽ ያደርጋል ታናሽ ብለን የምናልፈው ነው፡፡ በሀገርም በሀገር ወዳዶችም ላይ ተሰብስበው ነጋሪት የሚጎስሙት እነማን ናቸው ስንል ትላንትም ዛሬም የተረገሙ በሚለው የምንፈርጃቸው ባንዳና አንጃዎች መሆናቸውን እናያለን፡፡ ብዙዎቹ ለሆዳቸው ሲሉ ለወያኔም ያደሩ ነበሩ፡፡ ውሻ በበላበት ይጮሃል ሊባሉም ይገባል፡፡ ካድሬ ካልነበሩ አብሮ በላዎች ነበሩ፡፡ ስለዚህም ነግ ምን ይደረግ ስንል አለምንም ዋዛ ፈዛዛ፤ እነዚህን ተውሳኮች ማስወገድ፤ ከሕዝብ ጎራ ማራቅ፤ በምንም ምክንያት ቢሆን ጆሮም ፊትም አለመስጠትና በሚገባቸው ልክ መርገምም ማውገዝም ያስፈልጋል፡፡ የሕዝብ ጎራ ከጸዳ ትግሉን በቀና ማካሄድ ይቻላል፤ እባብን ከጉያ አቅፎና ተመርዞ መሽመድመድ እንጂ ምንም ፋይዳ አይገኝም፡፡ ጎራችን ከጸዳ መፈክሮቻችንን አስተካክለን ከዘረኞቹ ማደናገሪያ አጽድተን ለመሰባሰብና ለመታገል መጣር ቀዳሚ ግዳጃችን ይሆናል፡፡ የወያኔ ተለጣፊዎች ዛሬ ምንም ቢባል ቢለፈፍ የሕዝብ ወገን ሊሆኑ አይቻላቸውምና ሰልፋቸውን ከሃዲዎቹ አድርገን ልንወቃቸው ይገባል፡፡ ዘረኝነትንም በግልባጭ ዘረኝነት ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ለማቸነፍ መጣር እንዳለብን ለቅንጣትም መርሳት እንደሌለብን መገንዘቡም ወሳኝ ነው፡፡ የሕዝብ የሀገር አንድነት በኢትዮጵያዊነትና ዴሞክራሲ መሠረት፡፡ የወያኔ ኢህአዴግ ሥርዓት መወገድ ያለበት ነውና፤ ደም የተገበረው ይህን ግብ እውን ለማድረግ ነውና ዛሬ አገዛዙን ቀባብተውና አስመሳይ ለውጥ አድርገው ሊቀጥሉብን የተነሱትን ሰለባ ልንሆንላቸው አይገባም፡፡ ወያኔ ኢህአዴግ ይውደም ቋሚ መፈክራችን መሆን አለበት፡፡ ሁሉም እስረኞች ይፈቱ፤ የሽግግር ሂደት አሁኑኑ፤ ዘረኝነት ይውደም፤ ዘር የማጽዳትና የሕዝብ ፍጅት ይቁም፤ ...ወዘተ ማለት መቀጠል አለበን፡፡ የሕዝብ ማኅበራትም ነፃ ሆነው ህጋዊ ህልውናቸውን ማስረገጥ ይገባቸዋልና መደራጀታቸው ላይ ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ሴቶች ለመብታቸውና ለሀገራቸው ተደራጅተው አገዛዙንም ሆነ አድርባይ ሴቶችን እንዲታገሉ ይደራጁ ዘንድ ሰፊ ጥረት መደረግ አለበት፡፡ መንጋው በአገዛዙ እርዳታ ታጥቆም ተደግፎም ንጹሁን ሕዝብ ሲፈጅ ታይቷልና፤ አሁንም ዝግጅት አለውና ሕዝብ በራስ መከላከል እርምጃ ዝግጁ ሆኖም ሊገኝ ያስፈልገዋል፡፡ “ተኝተህ ተፈጅን አንቀበልም” ወቅታዊ አቅዋምኛ መፈክርም ነው፡፡ የዘረኞቹን ጎራ ለመከፋፈልና ለማዳከም፤ ቅራኔያቸውን ለማስፋት በስልት መንቀሳቀስ ያለብን ሲሆን ከሀገር ወዳድ ኃይላት ጎንም በጽናት መሰለፍ ወደ ጎን የማይደረግ ዋና ግዳጅ መሆኑም ሊታመንበት ያስፈልጋል፡፡

ሕዝብ ለሀገሩ ጸንቶ ከታገለ የሹሙና አገዛዙ እፍፍ፥ እፍፍ ያለ ድጋፍ አለጥርጥር ይተናል፡፡ ሹሙ ቢዋሽም ሕዝብን በዘር በሃይምኖት በቋንቋ የሚያገል እንጂ የሚያቅፍ ሥርዓት በሀገራችን የለም - ይህ ግልጽ በገሃድ የሚታይ ነው፡፡ ለሀገር ይጠቅማል የተባለው ሐቀኛ የፌደራል ሥርዓትም እስከ ዛሬ አልታየም፡፡ ወንጀለኞች በሁሉም መስክ ለፍርድ አልቀረቡም፤ ሙስና አላቆመም፤ አድልዎ አልሰከነም፤ ኢትዮጵያዊ ሠራዊትም ሊታይ አልቻለም፤ ምንም የተለወጠ ምንም የተጠቀምነው የለም፡፡ ይህ ነው ሐቁ፡፡ የዘረኛ፤ የባንዳ የሆድ አደርና አንጃ ግራንጃ ጫጫታ ሊያዳፍነው ያልቻለው የሐቅ ድምጽ ይህና ይህ ብቻ ነው፡፡

በኅብረት ለኢትዮጵያ እንታገል!

ወያኔ ኢህአዴግ በጋራ ትግላችን ይውደም!!

ድል ኢትዮጵያ ህዝብ ትግል !!